## ለ፳ኛው ምእተ ዓመት ፍጻሜ፣ ለ፳፩ኛው ምእተ ዘመን ዋዜማ፣ ዕንቊጣጣሽ መጣ ከሮማ

## ለሚሊኒየማችን ዕንቊጣጣሽ ሐወልታችን እንኳን ድኅና መጣሽ!!

*ሚሊኒየማችንን ለመቀበል በሀገር ደረጃ ብዙ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው። ስለዚህ በመጀመሪያ ከወዲሁ ለአዲሱ ዓመት፣ ለ፪ሺ ዓ/ም ዕንቊጣጣሽ በሰላም ያድርሳችሁ ያድርሰን በማለት ሰላምታየን ባቀርብ ወቅታዊ መስሎ ይሰማኛል። እንግዲህ ሚሊኒየማችንን የምናከብረበት እና እንደ ዕንቊጣጣሽ ልንጠቀምበት የሚገባን ከሮም ወደ ጥንተ መኖሪያው ወደ አክሱም ከተማ የተመለሰውን ሐወልታችንን ከወዲሁ ለማስታወስ ነው።*

## ክቡራንና ክቡራት ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሆይ!

***ያልታደሉ ኣንዳንድ ስሑታን እንደሚሉት ሐወልታችን የድንጋይ ቊራጭ ሳይሆን የብሔራዊ ማንነታችን ምልክትና ዘለዓለማዊው ቅርሳችን ነው። ይህንን በተመለከተ ትንሽ ለማከል ፍቀዱልኝ።***

***ታወሰኝ!!*** ***በ****November 23, 2004, Discovery News* ***ላይ “Italy Returns Stolen Obelisk to Ethiopia” በሚል*** *by Rossella Lorenzi* ***በተላለፈው ዜና “This is a Symbol of identity to Ethiopians” የሚለው ዐረፍተ ነገር እንደ አርዕስተ ዜና ተሰምሮበት ነበር።***

## ይህ ምን ማለት ነው?

As used to stand in Rome



(ሰርቀው ወስደው ሳያፍሩ በሮማ እንዲ ተክሏት ነበር)

*ሰዎች ወይም ነገሮች ሁሉ እያንዳንዳቸው ወይም በቡዱን ተለይተው የሚታወቁበት፣ ማለትም፣ አንዱ ከሌላው በውል የሚለይበት ልዩ-ልዩ ጠቃሽ አመልካች ምልክቶች አላቸው። አቶ እገሌ፣ ወይዘሮ እገሌ፣ የእገሌ ሀገር ሕዝብ ተብሎ ይታወቅበታል። በተለይ ሰው በአነጋገር፣ በአጠቃቀስ፣ በአለባበስ፣ በአረማመድ፣ በቁመት ወይም በደረት እና በመሠራው ሥራ ምክንያት…ወዘተ በመሳሰሉ ክስተቶችና ባህል ነክ ጉዳዮችም ማንነቱ ይታወቃል።*

*አገሮችም እንዲሁ በየትኛው ገፀ-ምድር ወይም መልክዐ ምድር እንደ ሚገኙ በማወቅ፣ በምልክቶች፣ በወንዝ፣ በባሕር፣ በሐይቆች፣ በተራሮች፣ በገደል፣ በሸንተረር፣ በሀገሩ በሰፈረው ሕዝብ ልዩ-ልዩ የሥራ ውጤቶች: - በሥልጣኔ፣ በጀግንነት፣ በዘመናዊነት፣ በጥንታዊነት፣ በሕዝቡ ብሔራዊ ፍቅር፣ በወኔ፣ የሕዝብ አንድነት እና ወዘተ ሀገሮች በሥም ተለይተው እገሌ ተብለው ይታወቃሉ። እነዚህ ምልክቶችም ተፈጥሮአውያንና ሰው-ሠራሽ ነገሮች እንደ ሥእል፣ ሥነ-ህንፃዎች፣ ቅርሳ-ቅርሶች፥ የብረታ-ብረት፣ የሸክላ እቃዎችና ከዕንጨት የተሰሩ፣ ልዩ-ልዩ ማሳሪያዎች እና ጌጣጌጦች ሊሆኑ ይችላሉ።*

*ኢትዮጵያ ሀገራችንም ኢትዮጵያ የሚያሰኟት ልዩ-ልዩ እና ብርቅ የጥንት ሥልጣኔዋን የሚያሳዩ ምልክቶች አሏት። እነሱም ሐወልት ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮ ያደላት ተራሮች፣ ወንዞችና ሸንተረሮች፣ በኅብረ-ብሔር ያጌጠ ሕዝቧ እና በሌላ ዓለም የማይገኙ ብርቅ እንስሳቷ እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።*

*አዎ! ኢትዮጵያ ኣህገራችን የራሷ የዘመን አቈጣጠር (Calendar) እንዲሁም የራሷ የሥነ-ጽሑፍና የፊደል ቅርፅ ያሏት ልዩ ሀገር ናት። በዚህና በመሳሰሉት ብርቅዮሽ ልዩ-ልዩ ጸጋ ኢትዮጵያ ተብላ ተለይታ ትታወቃለች። ራሳቸው ሳይንስቶች በመሰከሩት መሠረት፣ ኢትዮጵያ ብቸኛዋ በሌላ ዓለም የማይገኙ የሰው ዘር ቀሬቶች መገኛም ናት። በእነዚህ ምክንያቶች ጥንታዊት የሰው ዘር መገኛ ታሪካዊት ሀገር ናት። የማይካድ ቀደምትነቷና ታሪካዊነቷን ይበልጥ አጒልተው የሚያሳዩ ዋና-ዋናዎቹ ደግሞ እንሆ በአክሱም ጥንታዊት መዲናችን የሚገኙ ሐወልቶቿ ሕያዋን ምስክሮቿ ናቸው።*

*በአክሱም የሚገኙ ሐወልቶቻችን የሁላችን ኢትዮጵያውያን በሙሉ ልዩ የኢትዮጵያዊነት ማንነት ምልክት፣ የጥንታውያን አባቶቻችን ቅርስና የታሪክ አሻራ ከመሆናቸው ሌላ የነፃነትና የወኔ መግለጫ፣ የጥንታውያን አባቶቻችን የጥንቱ ሥልጣኔ እና የሥነ-ጥበብ፣ የሥነ-ህንፃዎችና ታሪካዊ ሥራዎች ሁሉ ዋና መግለጫ እንደሆኑ ዓለም በሙሉ ያውቀዋል።*

*በአክሱም የሚገኙት ሐወልቶች ለተመልካችና ለተማራማሪው ሁሉ ዕፁብ ድንቅ የሚያሰኝ ይሥነ-ተፈጥሮ ገጽታና ውብ መልክ አላቸው። እነዚህ ሐወልቶች እንዴት እንደዚህ በሰው እጅ ሊሠሩ ይችላሉ? በማለት ዕፁብ ድንቅ! ብሎ ከማሰብና ከመደነቅ በስተቀር ተመራማሪዎች ዕድሜ ልክ ቢመራመሩባቸውም ምሥጢሩ ሌላ አዲስ ምሥጢር እየወልደ ይኖራል እንጂ ሐወልቶቹ ማን እንደ ሰራቸው፣ ወይም መቸ እንደተሰሩ፣ ለምን እንደ ተሰሩ እና እንዴት እንደተሰሩ ማወቅ ያስቸግራል።*

*ይህ የኢትዮጵያ አምላክ ሲፈቅድ፣ ቀኑ ጠብቆ አንድ ቀን፣ ምሥጢሩን ለባለ ምሥጢሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይገለጥለታል። ስለዚህ ሐወልት በክብር መያዝ ያለበት ምሥጢራዊ የክብር ቅርሳችን ነው።*

*ሐወልት በቃላት ሊገለፅ የማይችል የኢትዮጵያ የሀገር ክብር እና ብዙ ሌሎች ቁም-ነገሮችን ያዘለ የታርካችን መሠረታዊ ቅርስ መሆኑን የተገነዘቡ ኤውሮጳውያን፥ በተለይም በወቅቱ በኢጣልያ የሀገር መሪ የነበረው ፋሽሽት በኒቶ መሶሎኒ፣ ከሐወልቶቻችን አንዱን መርጦ 1928 ዓ/ም ዘርፎ ወሰደብን።*

*ለምን ዘርፎ ወሰደው? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ማንኛውም ሰው በግምት እንኳ ሊመልሰው የሚችል ሳይታለም የተፈታ ምሥጢር ነው። የወሰደበት ምክንያት ጠቃሚ ቅርስ ከመሆኑም በላይ የታሪካችን አሻራ እና የኢትዮጵያዊነታችን ብሔራዊ መንነት መልያ ምልክት ስለሆነ፣ እሱ ቢወሰድብን ቀስማችን ተሰብሮ ወኔአችን ይዝላል፣ ብሔራዊ ኢትዮጵያዊ ክብራችን ይዋረዳል (ይቀንሳል)፤ ስለዚህ ሰጥ-ለበጥ ብለን እንገዛለታለን ብሎ ሰለአሰበ ነበር ሐወልታችንን የዘረፈው። ነገር ግን እንዳሰበው ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻቱንና ክብሩን ለመጠበቅ፣ ንብረቱን (ታሪካዊ ቅርሱን) ለማስመለስ ይበልጥ ታገለ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ታግሎም አልቀረ እንሆ ታሪካዊው የብሔራዊ ማንነቱ መለያ ቅርስ የሆነውን የተዘረፈውን ሐወልት ለማስመለስ ለ፷፰ ዓመታት ሳይታክት ታግሎ ለድል በቅቷል። ከዚህ የበለጠ ዕልል የሚያሰኝ ታላቅ ድል ኣይገኝምና በደስታ ልናስታውሰው ይገባናል።*

*በዚሁ አጋጣሚ ብሔራዊ ኢትዮጵያዊ ክብራችን እና ነጻነታችንን ለመጠበቅ <u>መሥዋዕተ ክብር</u> ለሆኑልን <u>ጀግኖች ወላጆቻችን</u> <u>ክብርና ዘለዓለማዊ ዝክር</u> ይሁን።*

*እንዲሁም የአባቶቻቸውን ወኔ ወርሰው ሐወልቱን ለማስመለስ ሌት ተቀን ለታገሉት፣ በሰላማዊና ዓለም-አቀፋዊ ዲፕሎማሲያዊ መንገድ፣ ብልኀነትና ጀግንነት በተላበሰ ጥበብና መላ ሓወልታችን እንዲመጣ ላደረጉልን የዛሬው <u>የሕዝብ ለጆች፣ ጀግኖች መሪዎቻችንም</u> ክብርና ምስጋና ይድረሳቸው፤ አሜን።*

*ጊዜው ሳይሆን መታደስ ያለበት እኛው ነን መታደስ ያለብን እና እንታደስ። በመታደስ ይህ የሚመጣው ሚሊኒየምም የሰላም ይብልፅግና እና የሥራ ዘመን ያድርግልን! በሰላም አብሮ ለመኖር እና ተባብሮ ለመሥራት የሚያስችል ልቡና ይስጠን፤ አሜን!!!*

*ኪዳነ ማርያም ግርማይ ከሳንዲያጎ፥ ካሊፎርኒያ*

# ሐወልታችን የድንጋይ ቁራጭ አይደለም

As used to stand in Rome



እሰይ! እሰይ እንኳን ደስ አለን፣ ኢትዮጵያውያን ሁላችን፤
የጋራ ንብረታችን፣ (እሰይ! ዕልል!)[፪ት] …አገሩ ገባ ሐወልታችን።

ሐወልት! ሐወልት ልዩ ምልክት የኢትዮጵያዊነት፤
የጥንቱ ሥልጣኔ የቅርሳችን አሻራ የታሪክ መሠረት፤
ከሥድሳ ሥምንት የስደት ዓመታት፤
እሰይ! እሰይ ዕልል! …አገሩ ገባ የአክሱም ሓወልት፤
ዕልል በሉ ጀግኖች ዕልል በሉ ሰማዕታት፤
በሐወልት ከበረ የሕይወት መስዋዕት። (፪ት ጊዜ)

የድንጋይ ቁራጭ አለመሆኑ ይኸው መሰከረ፤
የምሥራች አለ የራሱ ቋንቋ ተናገረ፤
እሰይ! እሰይ ዕልል! አገሩ ገባ ከብሮ አከበረ፤
ሰላም ይሁን አለ የምሥራች አበሰረ።

የነገሥታት መቃብር፣ የኢትዮጵያ ክብር፤
ተጠብቆ የኖረ በከርሰ ምድር፣ በሐወልቱ ሥር፤
እሰይ! ዕልል! ፈካ እንደ አበባ ይፋ ሆነ ምሥጢር፤
የድንጋይ ቁራጭ የተባለው ነገር፤
ከሮም እስከ አክሱም ሲከንፍ ታየ ሕያው ሆኖ ሲበር፤
ነጎደ እንደ ዖፈ-ንሥር፣ አገሩ ለመግባት ታሪክ ለመመስከር።

ኦ ሊቃውንተ አክሱም! ሰብሕዎ ለዘፈጠሮ …በጸናጽል ወበከበሮ፤
ሰላም አለ ሐወልት ጽዮንን አክብሮ፤
አገሩ ሲገባ ከስደት ኑሮ፣ የሰላም ዘመን ዘንድሮ፤
ለካስ ምሥጢር አለው የተወው ቀብሮ፤
ከባዕድ ከወራሪ ሰውሮ፤
ለጽዮን የሰጣት በአደራ አስመሥጥሮ።

ሐወልት ማለት ለካ'ስ እንዲህ ነው?
ሕያው ድንጋይ አምላክ ያከበረው፤
በእውነት ለእውነት ቀጥ ብሎ የቆመው፤
ገና የሚነግረን ብዙ ምሥጢር አለው።

ለጥንቱ ቤተ መንግሥት ዘወትር የሚቆም ታማኝ ዘብ፤
አንገቱን የሚሰጥ ለአሕዛብ።

የሀገር ምሥጢር አሳልፎ ከሚሠጥ ለባዕድ፤
መከራን መቀበል መረጠ መሰደድ፤
መብረቅ ቢበርቅ ነጎዳም ቢኖጉድ
አልተረበሸም የሓወልት ሆድ፤
ሌት ተቀን ታገለ አገሩ ለመሄድ።

አሁን ግን ከሥድሳ ሥምንት ዘመናት በኋላ፤
ከስደት ሲመለስ ወደ ዳዕሮ ዒላ፤
እሰይ ዕልል! አዋልደ ጽዮን ዕልል በላ።

ዕልል በሉ ዕልል! ዕልልል! ዕልልል! ዕልል፤
ዕልልል! ዕልል! ዕልል የደስታችን ቃል።